# የአቋም መግለጫ

እኛ የኢትዮጵያ  አርብቶአደሮች ከጥር 17-18 /2001 ዓ/ም በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሠመራ ከተማ ተገኝተን በብሄራዊ ደረጃ "**ስኬታማ ተግባሮቻችንን በአርብቶአደር አካባቢ በማስፋፋት የኢትዮጵያን ህዳሴ በጽኑ መሠረት ላይ እንገነባለን** በሚል መሪ ቃል የኢፌዲሪ መንግስት ጠቅላይ ሚኒስቴር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ፣ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት የልማት ጀግና አርብቶአደር ተሸላሚዎችና የልማት አጋሮቻችን ተወካዮች በተገኙበት ለ11ኛ ጊዜ በደመቀ ሁኔታ አክብረናል፡፡

ይህንን በዓል በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ጥረት ላደረጉ አካላትና አጋሮቻችንን ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋና እናቀርባለን ፡፡

በዚህ 11ኛው የአርብቶአደሮች በዓል ላይ የተገኘነው አርብቶአደሮች በዓሉን ባከበርንበት ወቅት በቀረበው የመንግስት ዝርዝር ዓመታዊ የአርብቶአደር አካባቢዎች የልማት የአፈጻጸም ሪፖርት ፣ የየክልሎቹ ምርጥ ተሞክሮዎች እና አሠራሮችን በመረዳት ከክቡር ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ጋር በመወያየት እንዲሁም በአፋር ክልል ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመስክ ተገኝተን ከተመለከትን በኃላ በቀጣይነት ሊተኮርባቸው ይገባል ባልናቸው ጉዳዮች ላይ በስፋትና በጥልቀት በመነጋገር የሚከተለውን **ባለ 11 ነጥብ** የአቋም መግለጫ አውጥተናል ፡፡

1. በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በመተግበር ላይ ያለው የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር መልካም ተሞክሮ በሌሎቹም የአርብቶአደር ክልሎችና አካባቢዎች በማስፋፋቱ ረገድ የፌዴራሉ እና የክልል መንግስታት ትኩረት እንዲሰጡ እንጠይቃለን፡፡

2. በአርብቶአደሩ አካባቢ የሚነሱ ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታትና ለመከላከል የሚያስችሉ የግጭት መከላከልና አፈታት እንዲሁም የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቶች ተጠናቀው ተግባራዊ እንዲሆኑ እንጠይቃለን ፡፡

3. አርብቶአደሩን በልማትና በመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ የሚያደርጉ የተጀመሩ የመሠረተ ልማት፣ የማህበራዊ አገልግሎት እና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እንጠይቃለን ፡፡

4. በአርብቶአደሩ አካባቢ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተጀመሩ ተስፋ ሰጪ የእንስሳት ሀብት ልማትን ማዕከል ያደረጉ የልማት ሥራዎች እንዲሁም በሰብልና እንስሳት ልማት ዙሪያ የተጀመሩ የአርብቶአደር ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ተጠናክረውና በምርምር ተደግፈው በስፋት ተግባራዊ እንዲሆኑ እንጠይቃለን ፡፡

5. የአርብቶአደሩ አካባቢዎች የተፈጥሮ ሀብት በተፈጥሮ ሰራሽና ሰው አመጣሽ ክስተቶች የተነሳ እየተመናመነ በመሆኑ መንግስት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ባህላዊና ዘመናዊ የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ ሥራዎች ተቀናጅተውና ተጠናክረው እንዲካሄዱ እንጠይቃለን፡፡

6. በአርብቶአደሩ አካባቢ ትምህርትን ለማስፋፋት እየተደረገ ያለውን ጥረት እያደነቅን በቀጣይነት የትምህርት ጥራቱንና ሽፋኑን ለማሣደግ ይረዳ ዘንድ ከአርብቶ አደሩ የአኗኗር ዘይቤ ጋር የተጣጣመ ሥርዓተ-ትምህርት ተቀርጾ ተግባራዊ እንዲሆን እንጠይቃን ፡፡

7. በአሁኑ ሰዓት ያለውን የገበያ እንቅስቃሴን ከዓለም አቀፍና ሃገራዊ የንግድ ሥርዓት ጋር ለማስተሣሰር እየተደረገ ያለውን በጐ ጅምርና ይህንኑ ከማገዝ አኳያ የተጀመረው ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን የማቋቋም ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን ፡፡

8. የፌዴራል መንግስት፣ የአርብቶአደርና የክልል መንግስታት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የአርብቶአደሩን የልማት ሥራዎች ከማጠናከርና የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከማሣካት አንጻር የተጀመሩ ጥረቶች ከመቼውም ጊዜ በላይ ትኩረት እንዲሰጣቸውና ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እንጠይቃለን።

9. የአርብቶአደሩን የቆዳ ስፋት ፣ የችግሩን ውስብስብነትና ያለውን ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ግምት ውስጥ በማስገባት አሁን እየተደረገ ያለው የበጀት ቀመር እና ምደባ እንዲሻሻልልን እንጠይቃለን ።

10. መንግስት የአርብቶአደሩን ልማት ለማሣደግ እያቋቋማቸው ያሉ ተቋማት እያደረጉ የአለውን ጥረት እናደንቃለን። ይሁን እንጂ ራሱን የቻለ የአርብቶአደር ተቋም መኖር ጠቀሜታው የጐላ በመሆኑ ይህንን አስመልክቶ የአሉትን ጠቃሚ አለምአቀፍና የአገር ውስጥ ልምዶች ተወስደው አግባብ ባለው መልኩ እንዲደራጅልን እንጠይቃለን።

11. እኛም አርብቶአደሮች ከመንግስታችን እና ከልማት ጉን አጋሮቻችን በቁርጠኝነት በመቆም ስኬታማ ተግባሮቻችንን አጠናክረን በማስፋፋት የኢትዮጵያን ህዳሴ በጽኑ መሠረት ላይ ለመገንባት ቃል እንገባለን ።

በመጨረሻም በ10ኛው የአርብቶአደር በዓል ላይ የፌዴራል ጉዳዩች ሚ/ር በዓሉን ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት ተረክቦ እንዲመራና እንዲያስተዳድረው በተወሰነው መሠረት ሃላፊነቱን ተረክቦ ማስተዳደር መጀመሩን እያደነቀንና እያመሰገንን በቀጣይነት የሚከበረውም የ12ኛው አርብቶአደሮች በዓል በዚሁ መልኩ በደመቀ ሁኔ ታ እንዲከበርልን እንጠይቃለን ።

**"ስኬታማ ተግባሮቻችንን በአርብቶአደር አካባቢ በማስፋፋት የኢትዮጵያን ህዳሴ በጽኑ መሠረት ላይ እንገነባለን"**

**ጥር 18/2001 ዓ.ም**

**ሠመራ**